# ትግሉ ሰው ጠይቋል! ሰዉም ትግል ናፍቋል!

ከአስረግደው ካሴ

እየቆጠቆጠ ያመመው ሁሉን፣
ሀገር መሳለቂያ መሳቂያ ብትሆን።
በጋራ በዱሩ ሲጠበቅ የኖረ፣
በሜዳው በጫካው ሲጠበቅ የኖረ፣
ትግል ከተማ ገብቶ አርፎ ተገሸረ፣
ትግል እግር አውጥቶ ወንዝ ተሻገረ።
ብለው ለሚሉቱ ወሬያቸውን ትቶ፣
ማስረግ ግዴታው ነው አዲስ መላ መቶ፣
በየቀበሌዋ በክፍለ ከተማው አንገት አስገብቶ።

ከእንግዲህ ቅጥረኛ!
ወይ! ከህዝቡ ያብር፣
ወይ ዝምብሎ ይኛ!
ማንፏቀቅ ዘበት ነው መሆን አላጋጭ፣
ህዝብ አልሆንም ካለ መብቱን አስረጋጭ።
ትግል ይገላምጣል ይቆጣል ፈሪን፣
ትግል ይገላምጣል አጎብጓቢውን፣
ትግል ይገስፃል በሰው ልጅ ሰቆቃ፣
አሽቃባጭ ቀላዋጭ ተግባሩ እንዲያበቃ።

ህዝብ እምቢኝ! ካለ ግፉ ከመረረው፣
እንኳንስ አሽርጋጅ ሌላም አይመልሰው።
እርገጣ ካባተ፣
ትግል ሰው ካሸተ፣
ወደው ባይፈልጉት ወደው ባይጠሩት፣
አመፅ ማዕበል ነው የማይገድቡት።

ለሆድ ተጠራርቶ፣
ህዝብን ትቶ ረስቶ፣
ከቅጥር ቢገባ፣
ታጋይ ይታዘባል እራሱን ሸጉጦ በግቢው አበባ።
አርበኛ ያውቀዋል የባንዳን ፈዘዞ፣
አይሞሻለቅም ለሱ ጠሩን ሰብቆ ጎራዴውን መዞ፣
ያስሮጠዋል እንጂ በቆመጥ ጠልዞ።

በፍፁም አይጥርም ከእንግዲህ በሁዋላ ነበርን አውርቶ ይሆናልን ሸጦ፣
ሊያሳምን ሊያግባባ ከፋሽስት አብሮ የበላን ሽልጦ፣
እዚያው እንደሸንኩርት እራሱን ይጨርስ ተልጦ! ተልጦ!
በአጉል ፕሮፓጋንዳ በቆርጦ ቀጥል፣
በሀሰት አስታሞ የለም ያገር ድል።
ትግሉ ሰው ጠይቋል፣

ሰዉም ትግል መርጧል።